# አንድ አምላክና ሰው !

## (አማኑኤል)

1. በዘጸ 22፡20 «ከእግዚአብሔር በቀር ለአንዳች አምላክ የሚሰዋ ፈጽሞ ይጥፋ»። የሚለው የመለከት አዋጅ ለጣኦት አምላኪዎች እጅግ የሚያስፈራ ነው።

2. በዘጸ 20፡3 በጽላቱ ላይ በገዛ ጣቱ የጻፈው ደግሞ፦ «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» በሚለው የመጀመሪያ ትዕዛዝ የቀናተኝነቱን ኃይል ያመለክታል።

የመለኮት ስምም አንድ ስለሆነ ስሙን በከንቱ የሚጠራውንም ከበደል እንደማያነጻው አስረግጦ ያስጠነቅቃል ቁ. 7።

3. በዘጸ 34፡14፦ «ስሙ ቀናተኛ የሆነ እግዚአብሔር ቅንዓት ያለው አምላክ ነውና ለሌላ አምላክ አትስገድ» ሲል ለሁለተኛና ለሦስተኛ አምላክ ስግደት ስለከለከለ ብቻውን ያለ ቀናኢ አምላክ ነው።

4. በዘዳ 6፡4፦ «እስራኤል (ነፍስ ያለው ሁሉ) ሆይ፤ ስማ፡ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፤ አንተም አምላክህን እግዚአብሐርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ» ይላል።

ይህ ትዕዛዝ፤ ልብም ሆነ ነፍስ ኃይልም ለሌላ አምላክ ሳይከፈል ለአንዱ አምላክ ብቻ አምልኮ እንዲያቀርብ ያስረግጣል።

5. በኢሳይያስ 42፡8 ደግሞ፦ «እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ስሜ ይህ ነው፤ ክብሬን ለሌላ፡ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም»። በማለት ቁጣውንና ቀናተኛነቱን ያስረግጣል።

6. በኢሳይያስ 43፡10፦ «ታውቁና ታምኑብኝ ዘንድ፤ እኔም እንደሆንሁ ታስተውሉ ዘንድ፡ እናንተ የመረጥኋችሁም ባሪያዬ ምስክሮቼ ናችሁ ይላል እግዚአብሔር፤ ከእኔ በፊት አምላክ አልተሠራም ከእኔም በኋላ አይሆንም። እኔ፡ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፡ ከእኔ ሌላም የሚያድን የለም» ይላል።

7. በኢሳይያስ 44፡8፦ «አትፍሩ አትደንግጡም፡ ከጥንት ጀምሬ አልነገርኋችሁምን? ወይስ አላሳየኋችሁምን? እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ። ከእኔ ሌላ አምላክ አለን? አምባ የለም፤ ማንንም አላውቅም»። በማለት በሰማይ ሁለተኛም ሆነ ሦስተኛ እንደሌሉ በቅንአቱ ቃል ያስረግጣል።

8. በኢሳይያስ 44፡24፦ «ከማኅፀን የሠራህ፡ የሚበዠህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ሁሉን የፈጠርሁ፤ ሰማያትን ለብቻዬ የዘረጋሁ ምድርንም ያጸናሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ፤ ከእኔ ጋር ማን ነበረ?» ሲል ይጠይቀናል። ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ እግዚአብሔር እንዳልነበረ የተረጋገጠ ከሆነ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ማለት ምንድር ነው? ትል ይሆናል (ይሆን)?

9. መልሱ፦ በ፩ጢሞ 1፡15-17 በግልጽ ይታያል። «ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው፡ ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ፡ ስለዚህ ግን፡ የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት በእርሱ ያምኑ ዘንድ ላላቸው ሰዎች ምሳሌ እንድሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ዋና በምሆን በእኔ ላይ ትዕግሥቱን ሁሉ ያሳይ ዘንድ፤ ምሕረትን አገኘሁ። ብቻውን አምላክ ለሚሆን ለማይጠፋው ለማይታየውም ለዘመናት ንጉሥ ምስጋናና ክብር እስከ ዘላለም ድረስ ይሁን፡ አሜን»። ካለ በኋላ በምዕ 2፡5-7 ደግሞ ተንትኖ አንድ አምላክ በሥጋ መገለጡን ሲያስረዳ፦ «አንድ እግዚአብሔር አለና፡ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፡ እርሱም <u>ሰው የሆነ ክርስቶስ</u> ኢየሱስ ነው፡ ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ፡ ይህም በገዛ ዘመኑ ምስክርነቱ ነበረ፤ እኔም ለዚህ ነገር አዋጅ ነጋሪና ሐዋርያ በእምነትና በእውነትም የአሕዛብ አስተማሪ ለመሆን ተሾምሁ፤ እውነት እናገራለሁ፤ አልዋሽም»። ሲል አንድ መንፈስና አንድ ሥጋ በውሕደት እንዳለ ያረጋግጣል።

10. በምዕ 3፡16 ደግሞ በግልጽ ሲናገር፦ «እግዚአብሔርንም የመምሰል ምስጢር ያለጥርጥር ታላቅ ነው፡ <u>እግዚአብሔር በሥጋ ተገለጠ፡ ይላል።</u> እግዚአብሔር መንፈስ ነው ሥጋና አጥንት የለውም። ሉቃ 24፡39። የሐዋ 4፡24 ሥጋና አጥንት ያልነበረው አንዱ አምላክ ሰውን ለማዳን ያቀደበት ዘመን ሲደርስ ቃሉን ሥጋ በማድረግ በሥጋና በደም በአጥንትም በሚዳሰስ አካል ተገለጠ፤ አማኑኤል ሆነ፡ በአካል በመካከላችን ተገኘ እንጂ ሁለት እግዚአብሔሮች አልሆነም። በዮሐ 1፡1-14 ላይ አንድነቱ ተረጋግጦአል። እግዚአብሔር ቃል ስለሆነ ቃልን ለማውጣ ችሎአል፤ መንፈስም በመሆኑ፡ መንፈስን እፍ እያለ ለሁሉም በማካፈል ይሰጣል። ኢዮብ 32፡8። 33፡4።

እየተከፈለ የሚሰጥ ደግሞ እስትንፋስ እንጂ አካል ሆኖ አፍንጫ ጆሮ እግር እጅ ሊኖረው አይችልም። የሐዋ.ሥራ 2፡1-4። ቁ. 17። ዮሐ 20፡22 ተመልከት።

በዮሐ ወንጌል 12፡44-45 <u>ክርስቶስ የአብ</u> የመንፈስና የሥጋም ውህደት መሆኑን ሲያረጋግጥ፦ «ኢየሱስም ጮኸ፡ እንዲህም አለ፦ በእኔ የሚያምን በላከኝ ማመኑ ነው እንጂ በእኔ አይደለም፡ እኔንም የሚያይ የላከኝን ያያል። ማለቱ የመንፈስ መልኩ ወይም መገለጫው ሥጋው መሆኑን ያረጋግጣል።

11. በዮሐንስ ወንጌል 1፡1-14 «<u>አስቀድሞ ቃል ነበረ፡</u> ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ <u>እግዚ አብሔርም ቃል ነበረ»</u> ይላል። በአሮጌው አማርኛና በግሪኩ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እግዚአብሔር ራሱ ቃል እንደነበረና ቃልም በውስጡ እንደነበረው ስለሚያረጋግጥ እግዚአብሔርና ቃል ምንጊዜም ለየብቻ የኖሩበት ጊዜ የለም። በሁለት አካላትም ተለያይተው የታዩበት ጊዜ የለም። እግዚአብሔር ቃል ባይሆን ኖሮ ቃልን ወልዶ ሥጋ ባላደረገውም ነበር።ቁ. 14።

ክርስቶስ ከዘላለም በቃልነት የኖረ እንጂ ከተፈጠረ 1989 ዓመት ሆነው የማይባልለት በመሆኑ፡ በሚክ 5፡2-4 «አንቺ ቤተልሔም ኤፍራታ ሆይ፡ አንቺ በይሁዳ አእላፋት ታናሽ

ነሽ፤ ካንቺ ግን በእሥራኤል አለቃ የሚሆን ይወጣልኛል። መውጣቱም ከጥንት ነው ከዘላለም ዘመን ይላል። ከጥንት ከዘላለም ዘመን የነበረው ቃል በማርያም ማሕፀን ሰው በመሆኑ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል። በመዝ. (33)፡5-6 «...ምድር በእግዚአብሔር ቸርነት ሞላች። በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ተሠሩ ሠራዊታቸውም ሁሉ ባፉ እስትንፋስ»። በማለት እግዚአብሔር በቃሉና በእስትንፋሱ እየፈጠረ ሕይወት መስጠቱንና አንድ እንጂ ሁለት ወይም ሦስት አካላት እንዳልነበሩት ያረጋግጣል።

12. ሐዋርያው ጴጥሮስም ሥጋ እንጂ መንፈስ እንደማይሞት ሲያረጋግጥ፦ «ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፤ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ» ይላል። ፩ጴጥ 3፡18

13. ቃል ሥጋ ሊሆን የተፈለገበት ዋና ምክንያት፦ 1ኛ. የመለኮት ሙላት ሁሉ በሥጋ ሰውነት ለዘላለም ሊኖር የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ ስለሆነ ነው። ቆላስ. 2፡9

2ኛ. የእግዚአብሔር የመገለጫ አካሉ ስለሆነ ነው። «እርሱ በዚህ በኋለኛው ዘመን በልጁ ነገረን። ሁሉን ወራሽ ባደረገው። ዓለሙንም በርሱ የፈጠረ። እርሱም የክብሩ ብርሃን የአካሉም ምሳሌ ሁሉንም የያዘ በችሎቱ ቃል» ይለናልና። ዕብ 1፡2-3

በቆላስ. 1፡15 «እርሱም (ክርስቶስ) የእግዚአብሔር ምሳሌ የማይታይ የፍጥረት ሁሉ መጀመሪያ። ነገር ሁሉ በእርሱ ተፈጥሮአልና በሰማያት ያለ ሁሉ በምድርም ያለ የሚታይ የማይታይም መናብርትም (ዙፋናት) እጋእዝትም ሊቃናትም ስልጣናትም ሁሉ በእርሱ ለእርሱም ተፈጠረ»። በማለት አንዱ ፈጣሪ በቃልነትም በመንፈስነትም ያለ የነበረ የሚኖርም መሆኑን ያረጋግጣል። ቃል ሥጋ ሆነ ሲባል መንፈስ ሥጋ ሆነ ማለት አይደለም። የመንፈሱ ቃል ሥጋ ሆነ ማለት ነው እንጂ።

3ኛ ምክንያት፦ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሕመምና ሞት ትንሳኤም ከጥንት ያቀደውን የማዳን ተግባር ለመፈጸም ስለፈለገ ነው። ፪ቆሮ 5፡18-19።

አንዳንድ ሰዎች ክርስቶስ ከአብ ውጪ ሆኖ የጸለየ፤ ያለቀሰና የጮኸ መስሎአቸው ሁለት በተለያየ ቦታ ያሉ አካላትን ይፈጥራሉ።

14. በእግዚአብሔር ቃል የተጻፈውን እናስተውል፦ «ነገር ግን የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን ከእግዚአብሔር ነው እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር...» ፪ቆሮ5፡18-19 በማለት አስታራቂም ታራቂም ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያረጋግጣል። በሐዋ.ሥራ 20፡28 ላይ፦ እግዚአብሔር በገዛ ደሙ ቤተ ክርስቲያንን እንደገዛ ያረጋግጣል ስለዚህ እግዚአብሔር አብ በገዛ ሥጋው በገዛ ደሙ እኛን እንዳዳነ ከተረጋገጠ መንፈስና ሥጋ፤ ደም አንዱ አምላክ እግዚአብሔር ነው ማለት ነው። «እግዚአብሔር በሥጋ ተገለጠ ይላል እንጂ በሁለተኛው እግዚአብሔር ተገለጠ» አይልምና።

አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ወደ ሰማይ እያየ የጸለየው አባቱ ሰማይ ልጁ በምድር ቢሆኑ አይደለምን? ይላሉ።

15. መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ምን ያስተምራል? በዘዳ 32፡39-40 «አሁንም እኔ ብቻዬን፤ እኔ እንደሆንሁ፤ ከእኔም በቀር አምላክ እንደሌለ እዩ፤ እኔ እገድላለሁ አድንማለሁ፤ እኔ እመታለሁ፤ እፈውስማለሁ፤ ከእጄም የሚያድን የለም። <u>እጄን ወደ ሰማይ እዘረጋለሁና፤</u> እንዲህም እላለሁ፤ ለዘላለም እኔ ሕያው ነኝና»። በማለት ይህ አንዱ አምላክ እጁን ወደ ሰማይ እንደሚዘረጋ ያስረዳል፤ ወደማን ይዘረጋል?

እንደዚሁም በአዲስ ኪዳን ዘመን ያለው አንዱ ኢየሱስ ስለአንድነቱና ሰማይንና ምድርን የሞላ መሆኑን ስለ ራሱ ሲመሰክር፦ «ስለምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ ካላመናችሁ ስለሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ? ከሰማይ ከወረደው በቀር ወደሰማይ የወጣ ማንም የለም፤ እርሱም በሰማይ የ..ኖረው የሰው ልጅ ነው» ይላል። ዮሐ. 3፡13

ክርስቶስ በሰማይም በምድርም በሙላት የነበረ እንደሆነ እና አምላክም ሰውም ብቻ መሆኑን ያረጋግጣል። አንድ አምላክ በሥጋ አካል የተገለጠ ብቻውን ያለ ኢየሱስ ነው። ይሁዳ ቁ. 3-4፤ ቁ. 25። በራእይ 1፡8፤ ቁ. 17-18 «ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ፤ አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ»። ያለው ኢየሱስ አንዱ አምላካችን ነው፤ ሞቶም የነበረ ከዘላለም እስከ ዘላለም የነገሠ እርሱ ብቻ ነው።

16. በራእይ 4፡2 በሰማይ አንድ ዙፋንና አንድ ተቀማጭ ብቻ እንዳለ ያረጋግጣል።

በራእይ 4፡8-11 ጌታችንና አምላካችን እያሉ አክሊሎቻቸውን በእግሩ ሥር ሲያስቀምጡና ሲያነግሡት ይታያል።

17. በራእይ 5፡6-14 በዙፋኑ ላይ የተቀመጠውም ሆነ እንደታረደ በግ የቆመው ራሱ በበግ የተመሰለው ጌታና አምላክ እንደሆነ፦ «በረከትና ክብር ምስጋናም ኃይልም ከዘላለም እስከ ዘላለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለበጉም ይሁን»። በማለት ያስረግጣል። ራእይ 5 ቁ. 13

18. በራእይ 7፡10 በዙፋኑ (ነጠላ) ለተቀመጠው ለአምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው በማለት በአንድ ዙፋን ላይ የተቀመጠው አምላክና ሥጋ ወይም አምላክና ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ያረጋግጣል።ያዕ 2፡19። ዮሐ 14፡6-10። ያንብቡትና አንድነቱን ያረጋግጡ።

## ለተጨማሪ ማብራሪያ

http://www.sayadi-al-nas.com